## የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ሀሳብ

### መግቢያ

ይህ የማሻሻያ ሀሳብ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013፣ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1240/2013፣ ለሕዝብ የሚሸጡ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ የማድረግ መመሪያ ቁጥር 1047/2025፣ ሠነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዝብ የማቅረብና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2024 እንዲሁም የማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት የአሠራር ደንቦችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ነው::

| ተ.ቁ | የተሻሻለው አንቀጽ | የቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ድንጋጌ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 1 | **አንቀጽ 4** የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) | አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጾች 4.1 እና 4.2 እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡-<br>4.1. የአክሲዮን ማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 2,000,000,000.00 (ሁለት ቢልዮን ብር) ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) ዋጋ ባላቸው ተራና የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው::<br>4.2. ከተፈረመው ካፒታል ውስጥ ብር 1,877,003,163.82 በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል:: | የወቅቱን የፋይናንስ መረጃ መሠረት በማድረግ የተሻሻለ ድንጋጌ:: |
| 2 | **አንቀጽ 5** የአክሲዮን ይዞታ ገደብ | አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-<br>5.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አዳዲስ አክሲዮኖችን ለሽያጭ በሚያወጣበት ጊዜ አንድ ባለአክሲዮን ሊገዛ የሚችለውን አነስተኛ የአክሲዮን መጠን ሊወስን ይችላል:: | በካፒታል ገበያ አሠራር መሠረት ቦርዱ ዝቅተኛውን የግዢ መጠን የመወሰን ሥልጣን እንዲኖረው ለማድረግ የቀረበ:: |
| 3 | **አንቀጽ 8** ስለ አክሲዮኖች አወጣጥ፣ ምዝገባ እና ክፍያ | ከንዑስ አንቀጽ 8.6 ጀምሮ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች ተካተዋል፡-<br>8.6. አክሲዮን ማኅበሩ አክሲዮኖችን ከተጻፈባቸው መደበኛ ዋጋ (Par Value) በታች መሸጥ አይችልም::<br>8.7. አክሲዮን ማኅበሩ በሕግ በተፈቀደውና በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወሰነው የካፒታል ጭማሪ መሠረት አክሲዮኖችን ከተጻፈባቸው መደበኛ ዋጋ በላይ (At Premium) ለሽያጭ ማቅረብ የሚችል ሲሆን፤ የሽያጭ ዋጋውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ይወስናል::<br>8.8. ሙሉ በሙሉ የተከፈሉ አክሲዮኖች በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ከተመዘገቡ በኋላ ወደ ባለአክሲዮኑ በማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት የኤሌክትሮኒክስ ሂሳብ ገቢ ይደረጋሉ::<br>8.9. ለአዲስ አክሲዮኖች ግዢ የተደረገ ክፍያ አግባብነት ባላቸው ሕጎችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸም አለበት::<br>8.10. የተፈረመ የአክሲዮን ባለይዞታ፣ ነባር ባለአክሲዮን እና የአላባ ጥቅም መብት ያለው ማንኛውም ሰው፣ በንግድ ሕጉና በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን መመሪያዎች መሠረት | የአክሲዮን አወጣጥን፣ ከተጻፈበት ዋጋ በላይ መሸጥን፣ የምዝገባ ሂደት እና ያልተከፈሉ አክሲዮኖችን ኃላፊነት በተመለከተ የተደጋገሙ ሀሳቦችን በማስወገድ በአንድ አንቀጽ ሥር ተደራጅቷል:: |

| ተ.ቁ | የተሻሻለው አንቀጽ | የቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ድንጋጌ | ማብራሪያ |
| --- | --- | --- | --- |
| | | ተፈርመው ያልተከፈሉ አክሲዮኖችን ክፍያ ለአክሲዮን ማኅበሩ በአንድነትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡<br>8.11. ዋጋቸው ያልተከፈለ አክሲዮኖች ቀሪ ክፍያ ጥሪ ከተደረገ በኂላ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለ፣ የንግድ ሕግ አንቀጽ 289 ንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (7) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ | |
| 4 | አንቀጽ 12 የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ-አልባ መሆን | በነባሩ የመመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ ስለ ወረቀት የአክሲዮን ምስክር ወረቀቶች አሰጣጥ፣ መተካት፣ መጥፋት ወይም መበላሸት የሚደነግጉ ማንኛቸውም አንቀጾችና ንዑሳን አንቀጾች ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል፡፡<br>አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጾች 12.1 እስከ 12.8 እንደሚከተለው ተተክተዋል፡-<br>12.1. በአክሲዮን ማኅበሩ የሚወጡ ሁሉም ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ሙሉ በሙሉ ግዑዝ-አልባ በሆነ መልክ ብቻ የሚወጡ ሲሆን፣ አክሲዮን ማኅበሩ ምንም ዓይነት የወረቀት የአክሲዮን የምስክር ወረቀት አይሰጥም፡፡<br>12.2. የሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለቤትነት፣ ዝውውር፣ በዋስትና ማስያዝ፣ ወይም ከአክሲዮኖች ጋር የተያያዙ ማንኛቸውም ግብይቶችና መብቶች የሚረጋገጡት በማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በሚያዘው የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ብቻ ይሆናል፡፡<br>12.3. የወረቀት የአክሲዮን ምስክር ወረቀቶች የባለቤትነትን፣ የዝውውርን፣ በዋስትና ማስያዝን ወይም ክፍያ የመጠየቅ መብትን ለማረጋገጥ ሕጋዊ ተፈጻሚነትና ዋጋ አይኖራቸውም፡፡<br>12.4. አክሲዮን ማኅበሩ በዋና መሥሪያ ቤቱ ከማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መዝገብ ጋር የሚናበብ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ይይዛል፡፡<br>12.5. መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN)፣ የብሔራዊ መታወቂያ/ፓስፖርት ቁጥር፣ የተፈረመና የተከፈለ የአክሲዮን መጠን እንዲሁም የድምፅ መስጠት መብትን የያዘ መሆን አለበት፡፡<br>12.6. በማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መዝገብ እና በአክሲዮን ማኅበሩ መዝገብ መካከል ልዩነት ከተገኘ፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ወይም የተወከለው ኃላፊ ስህተቱ በታወቀ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ከግምጃ ቤቱ ጋር በመተባበር የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡<br>12.7. መዝገቡ ማንኛውም ባለአክሲዮን እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው ሊመለከተው እንዲችል ሆኖ በአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ለረጅም ጊዜ በሚቆይ መልኩ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተይዞ በመደበኛ የሥራ ሰዓታት ሁሉ ክፍት ሆኖ ይቀመጣል፡፡ | በመመሪያ ቁጥር 1047/2025 መሠረት የወረቀት አክሲዮኖችን ሙሉ በሙሉ በመሻር ኤሌክትሮኒክ የምዝገባ ስርዓትን አስገዳጅ የሚያደርግ ድንጋጌ፡፡ የባለአክሲዮኖች መዝገብ አያያዝንም ያጠቃልላል፡፡ |

| ተ.ቁ | የተሻሻለው አንቀጽ | የቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ድንጋጌ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| | | 12.8. ባለአክሲዮኖች እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም የመዝገቡን ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሑፍ እንዲሰጠው አክሲዮን ማኅበሩን መጠየቅ ይችላል:: | |
| 5 | **አንቀጽ 13** የአክሲዮን ዝውውርና ግብይት | አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጾች 13.1 እስከ 13.7 እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡-<br>13.1. የአክሲዮን ማኅበሩ አክሲዮኖች የሕዝብ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች በመሆናቸው፣ በተፈቀደለት የሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በኩል ያለምንም ገደብ በነፃ ይተላለፋሉ:: የዚህ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 6 እና አግባብነት ያላቸው ገደቦች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::<br>13.2. በሁለተኛ ደረጃ ገበያ ግብይቶች (Secondary Market) በሚደረጉ የአክሲዮን ነፃ ዝውውሮች ላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ ቅድመ-ፈቃድ ወይም የነባር ባለአክሲዮኖች ቅድሚያ የመግዛት መብት ገደብ ተፈጻሚ አይሆንም::<br>13.3. ማንኛውም የአክሲዮን ዝውውር፣ በዋስትና ማስያዝ ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚደረግ መብት ማስተላለፍ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው በማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ላይ ሲመዘገብ ብቻ ይሆናል::<br>13.4. በሕግ ወይም ሥልጣን ባለው አካል ገደብ ከተጣለበት በስተቀር በባለአክሲዮኑ ስም ተይዞ ገዑዝ-አልባ የተደረገ የሠነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ላይ ምንም ዓይነት ክልከላ አይደረግበትም::<br>13.5. አንድ ባለአክሲዮን በሚሞትበት ጊዜ አክሲዮን ማኅበሩ በባለአክሲዮንነት የሚቀበላቸው በፍርድ ቤት አክሲዮኑ እንዲተላለፍላቸው የተወሰነላቸውን ነው::<br>13.6. አክሲዮኖችን በጋራ ከያዙ ባለአክሲዮኖች መካከል አንዱ ቢሞት የሟች የአክሲዮን ድርሻ ላይ መብት የሚኖራቸው በሕይወት የሚገኘው (የሚገኙት) የሟቹ ወራሽ/ወራሾች ይሆናሉ::<br>13.7. ማንኛውንም ሰው ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ሊያደርግ የሚችል የአክሲዮን ዝውውር በአክሲዮን መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት:: | የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1240/2013ን መሠረት በማድረግ የተደጋገሙ ንዑሳን አንቀጾችን በማቀናጀት የተቀናጀ አንቀጽ:: |
| 6 | **አንቀጽ 18** በጉባኤ ለመሳተፍ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ስለመመዝገብ | አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 18.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-<br>18.1. አዲስ የተመዘገቡ ባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመሳተፍና ድምፅ ለመስጠት በማዕከላዊ ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የኤሌክትሮኒክስ የምዝገባ ደብተር ላይ ጉባኤው ከሚካሄድበት ዕለት ቢያንስ 3 (ሦስት) ቀናት አስቀድመው የተመዘገቡ መሆን አለባቸው:: | የጉባኤ ተሳትፎና ድምፅ የመስጠት መብት ማረጋገጫ የምዝገባ ጊዜ ገደብ ድንጋጌ:: |

| ተ.ቁ | የተሻሻለው አንቀጽ | የቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ ድንጋጌ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 7 | **አንቀጽ 24** የቦርድ አባላት ቁጥር | ንዑስ አንቀጽ 24.1 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡- <br> 24.1. አክሲዮን ማኅበሩ ቢያንስ ዘጠኝ (9) የቦርድ አባላት/ዳይሬክተሮች ይኖሩታል:: | የቦርድ አባላት ዝቅተኛ ቁጥርን የሚያረጋግጥ ድንጋጌ:: |
| 8 | **አንቀጽ 26** የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር በካፒታል ገበያ ጉዳዮች | ከዚህ ቀደም ከተገለጸው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን (26.18)በተጨማሪ የሚከተሉት አዳዲስ ንዑስ አንቀጾች ተካተዋል፡- <br> 26.18. የአክሲዮን ማኅበሩን ሠነደ ሙዓለ ንዋዮች በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዘንድ የማስመዝገብ፣ በኢትዮጵያ ሠነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም በተፈቀደ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ የመመዝገብ፣ አክሲዮኖችን ለነባር ባለአክሲዮኖች ወይም ለሕዝብ ለሽያጭ የማቅረብ፣ የሽያጭ ዋጋና ጊዜ የመወሰን እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን ማረጋገጫዎችና ውሳኔዎች የመስጠት ሥልጣን፤ <br> 26.19. በተቆጣጣሪ አካላት የተቀመጡ የመረጃ ይፋ ማድረግ፣ የሪፖርት አቀራረብና የኮርፖሬት አስተዳደር ግዴታዎች እንዲሁም የካፒታል ገበያ ሕጎች ሙሉ በሙሉ መከበራቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት፤ <br> 26.20. በካፒታል ገበያ እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ሕጋዊና ስትራቴጂካዊ ውሳኔዎችን የመስጠት፣ እርምጃዎችን የመውሰድና ማኅበሩን የመወከል ሙሉ ሥልጣን:: | የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና መመሪያ ቁጥር 1030/2024 ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን የቁጥጥር፣ የውሳኔና የሕግ ኃላፊነቶች ግልጽ በሆነ መልኩ ለማካተት የቀረበ:: |

**አስተያየትዎን በኢሜይል አድራሻ info@hibretinsurance.com፣ በጽሑፍ በአዲስ አበባ ከተማ በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ በሚገኘው የሕብረት ኢንሹራንስ አ.ማ. ዋና መሥሪያ ቤት (የአክሲዮን ማኅበሩ ጸሃፊ ቢሮ 10ኛ ፎቅ) በአካል በመቅረብ፣ በድረ-ገጽ www.hibretinsurance.com ወይም በስልክ ቁጥር +251 11 126 34 34 በመደወል ማቅረብ ይችላሉ::**